በስመ አብ ወወልደ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ ብየ ይቺን መልእክት ስልክላችሁ የእዚብሔር በረከቱና ፀጋው አይለያችሁ በማለት ነው፣ እናንት እውነተኛ የእግዚአብሔርን መንገድ እንድንከተልና ካለሱ በቀር ሌላ አምላክ እንዳናመልክ እና ከሱ በቀር ሌላ የምናመልከው መኖር እንደሌለብን የምታስተምሩን ትምህርት ስጋን አልፎ አጥንትን ቦርቡሮ በመግባት ከሰውነቴ ክፍል ጋር ስለተዋሃደ የእግዚአብሔር ስም በተነሳ ቁጥር እናቱ ርቃ ስትሄድበት እንደሚያለቀስ ልጅ እንባየ ሳላስበው የወርዳል፤ ይህ ሁኔታየ ደሞ የበለጠ ለእግዚአብሔር ፍጹም እንድሆን እና የሱ አገልጋይ እንድሆን ያበረታታኛል።

ውድ ወገኖቼ ሆይ! አሁንም ነገም ከነገወዲያም ይህ የያዛችሁት በጐ ምግባር እና ብሩህ አመለካካት እንዳይለያችሁ አደራ እያለኩ እግዚአብሔር እጅግ አብዝቶ ይባርካችሁ እያልኩ ሳልመርቃችሁና ሳላመሰግናችሁ አላልፍም፤ ለወደፊትም ደካማው ህበረተሰብ ከአባያ ጠንቋይ፣ ከአጭበርባሪ ባለውቃቢ ነኝ ባይ፣ ከአታላይ ቃልቻ ባጠቃላይ በአምልኮ የሚያምኑትን ሰፊ ትምህርት እየሰጣችሁ አምዳችሁን በማስፋት እንደምታስተምሩን በሙሉ እምነቴ ስገልጽላችሁ በልበ ሙሉነት ነው፤

እንደነ አቶ ሚካኤል የመሰሉትን የአውልያ በሪያዎች እና ሰጋጅ አቀንቃኞች በዚህ ትምህርታችሁ ወደ በጐ ምግባር እንደምትመለሱዋቸው እመነቴ ነው፤ በእርግጥ አቶ ሚካኤልን በአይኔ ስላየሁ ስም ጠቀስኩ እንጂ በርከት ያሉ ባለሥልጣናትም ሆኑ ድሃው ሠርቶ አደር በዚህ እኩይ ተግባር እንደ ተበረዘ ያደባባይ ሚስጥር ነው፣ ሆኖም የናንተ አይነት የነቃና የበቃ እግአዚብሔርን ከልብ የሚያገለግል ሳይሰለችና ደከመኝ ሳይል ማስተማሩን ከቀጠለ፣ እንደ ታምራት ገለታ የመዋረጃና የመሳቂያ ቀናቸው እሩቅ አይሆንም፣ እግዚአብሔር ታጋሽ ነው፣ ርኅሩህና መሃሪም ነው፣ ከልብ አጥፍቻለሁ ይቅር በለኝ ቢሉት ይቅርታዉን አይነፍጋቸዉም፣ ሆኖም ለይቅርታ የሚደርሱትም ሆነ ከጥፋታቸው የሚማሩት አሃዱ አምላክ ብለው፣ በአንድ አምላክ ሲያምኑና ካለኔ በስተቀር ሌላ አምላክ አታምልክ የሚለዉን የእግዚአብሔርን በረከት እናንተ ስታስምሯቸው ነውና በርቱ እላለሁ።

እኔ ስለ እግዚአብሔር ብዙም አልከታተልም ነበር፣ ዛሬ ግን በፆም በፀሎት ሳርቀው ይኸው ለዚህ ትልቅ የሆነ መሠረት ከነቤተሰቤ ደርሻለሁ፣ ወደፊትም እሱ በረከት አይለየኝ አሜን፤ አንድ በኮንፒዩተር የተካነ ባለሙያ ወዳጄ የዛሬ ሁለት አመት የላከልኝን መልእክት ሳስበውና መለስ ብየ ስቃኘው፣ የሚመካ በእግዚአብሔር ብቻ ይመካ የሚለው ጥቅስ እጅግ ስለሚማርከኝና ስለምወደው እናንተም እንድታዩት በAttachement (በቋጠሮ) ልከላችኋለሁ፣ እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን የሚለዉን ግን የት እንዳደረኩት ጠፍቶብኝ ነው በቅርቡ ፈልጌ እልክላችኋለሁ።

በተረፈ ለምትሰጡት ሰፊ አገልግሎትና የተባረከ እይታና ራዕይ እግዚአብሔር ብርታቱንና በረከቱን ይስጣችሁ እያልኩ እሰናበታለሁ።

ተሰማ አሊ ነኝ

ከለንደን፤